የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፣ገበሬ፣ነጋዴ፣ወታደር፣ምሁር—
ወብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም፡፡

- ቁጥር 35 ቀን 25/4/68

ስ"ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት":

ወይንስ

ለነቃ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ የህዝብ ትግል

የየካቲት 1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦችን አብዮታዊ የትግል ትጥቅ ለማስፈታት ፊውዳሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች እስካሁን ድረስ ያልገለበጡት ድንጋይ፣ ያልመነሰሩት ሴራ የለም፡፡ እነዚህን ልዩ ልዩ ሴራዎችና ተንኮሎች እያከሸፈ የጭቁኖች ትግል አገሪቱን ቢያጥለቀልቃትም፣ አድሃሪ ሃይሎች የኢትዮጵያን ህዝብ ትጥቅ ለማስፈታት፣ ወይ ደግሞ እነሱ እያሉ በሁለተኛ ደረጃ በሚታዩ ጠላቶች ላይ በማስነሳት ትግሉን ለማዳከም፣ ተራማጆችን ለመከፋፈል፣ ከማሴር አልተቆጠቡም፡፡ ነገሩ የመደቦች ትግል ነውና ባገኙት ዘዴ ህዝቡን ለማዳከም፣ ትግሉን ለማቀዛቀዝ፣ ወይም የተሳሳተ አቅጣጫ ለመስጠት ቢሞክሩ አይገርመንም፡፡

የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ግን የፊውዳሊስቶቹንና የነሲአይኤን ሴራ ተራ በተራ እያከሸፈ ይወጣቸዋል፡፡ዞሮ ዞሮም በጠላቶቹ ላይ ሙሉ ድልን ይጎናፀፋል፡፡በዚህ ትግል ውስጥም ፀረህዝብ ሃይሎች የተራማጅ ካባ ደርበው፣ አንዳንዶም አልፈው ተርፈው በገናናዎቹ በነሌኒንና በነማርክስ ስም.እየማሉና እየተገዘቱ፣ ለማወናበድ ይሞክሩ ይሆናል፡፡ግን ሃቀኛ ማርክሲስቶች ደግሞ ቆልተዋል፡፡ ስለዚህ በአብዮት ስም አብዮቱን ለማጨናገፍ የሚሞክሩ አወናባጆችም ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ፡እየተጋለጡ እንደሚሄዱ ግልጽ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ተራማጆች መሃከል መከፋፈልን ለማጠንከር፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ዋና ጠላቶቻቸውን ችላ እያሉ ባልሆነ አቅጣጫ እንዲታገሉ፣ የድሎቻቸውን ጉዳና እየተው በሌላ በማይገኝ አቋራጭ እንዲጓበኩ፣ የጠለማው ዘመን እንዲራዘም የሚፍጨረጨሩ የንኡስ ከበርቴያዊ ደገፊዎች ልሳን የሆነው "ዲሞክራሲያ" የሚነዛውን መርዝ መዋጋት አስፈላጊ ሆኖ ያገኘነው ለዚህ ነው፡፡ፀረዲሞክራቲኩን የደርግ አገዛዝ እንደጊዜው ዋና ጠላት በመቁጠር የኢትዮጵያንጭቁን ህዝቦች የደም እንባ ሲያስለቅሱአቸው የነበሩትንና አሁንም የሚያስለቅሱአቸውን ፊውዳሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች አኩሉ እንዲዋጉ የሚጋብዛቸውን የዚህን ጋዜጣ ቁጥር 23 በሰፊው ህዝብ ድምጽ ቁጥር 33 ተችተንበት የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ፀረዲሞክራቲኩን ደርግ እየተዋጉ፣ የሱንም ፀረዲሞክራቲክ አገዛዝ እየታገሉ፣ አመዛኙን ጉልበታቸውንና ሃይላቸውን ዋና ጠላታቸው ላይ እንደሚያሳርፉ፣ ማዋልም እንዳለባቸው አብራርተናል፡፡ይህንን አድሃሪ ጉራም እንደማገበሳ ገልፀናል፡፡

በዚህ ቁጥራችን፣ እነዚህ በነማርክስና በነሌኒን ስም የተደባለቁትን ንኡስ ከበርቴ ደገፊዎች የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦችን የትግል ትጥቅ ለማስፈታት እንደበገሳት አንጠልጥለው የያዙትን የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸውን ጉዳይ አንስተን እንተቻለን፡፡አድርባዮቹ የዲሞክራሲያ አዘጋጆች፣ የልባቸውን በኢሰበረይ ጠልከተን "ተራማጅነታቸውን" ካላረጋገጥን በስተቀር በዚህ ጉዳይ ወርሰው ከአስቀወሰን — መንገሻ በዎም፣ ከነሲአይኤ ጋር እንደተሰለፉ እናሳያለን፡፡ከዚህም አልፈን እንሄዳለን፡፡አድርባዮቹ ለዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጉዳይ አንድ ሙሉ ቁጥር አውለዋል፡፡ በዚህ ቁጥራቸው ላይ ሰልፋቸው ከፀረህዝብ ሃይሎች ጋር እንዳይደለ ለማሳየት በሩስያ አብዮት ጊዜ እነሌኒን የወሰዱት አቋም ልክ እንደኛው ነበር እያሉ ለርካሽ አላማቸው የገናናዎቹን በለሸቪኮች ስም ለመበከል ሞክረዋል፡፡ስለዚህ እኛም ወደታሪክ ጠልሰን የነዚህን አድርባዮች የተንኮል ችሎታ ዝርነትና፣ የማወናበድና የማጭበርበር ሊቆነታቸውን ለአንባቢ እያሳየን እናጋልጣቸዋለን፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ይህ የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጉዳይ በዙ ሃቀኛ ተራማጆችን ያወናበደ ጉዳይ ነው፡፡በዚያው ልክ ደግሞ አድሃሪ ክበሉ፣ ፀረህዝብ ክበሉ፣ አወናባጅ ክበሉ ምርጫ እንዲደረገና ፀረዲሞክራቲኩ ደርግ ተወግደ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም የማይጠይቅ የለም፡፡

ባለፈው በሀዳር ወር ከነአስፋወሰን —መንገሻ ስም በስተቀኝ አለሁ የምትል አንዲት ''ፀረደርግ ገስጋሽ ንቅናቄ ኢትዮጵያን ከጉግማንጉግ ለማዳን'' የተባለች የደንቆሮ ፊውዳሊስቶች ንቅናቄ በ በተነቻው ወረቀት ላይ ጉግማንጉግ ደርግ ተወግዶ ህዝቡ በሚመርጣቸው ሲቪሎች እንዲተዳደር ትጠይቃለች::ይህ ጥያቄ ግን የሷ ብቻ አይደለም::

''አንድ የእድገት ደረጃ እንደተደረሰ፣ የቀድሞው ስርአት መዋቅር ፋይዳቢስነት ለሁሉም ግልጽ ይሆናል::ሁሉም አብዮት ይላል::በዚህ ጊዜ ያለው ተግባር ይህንን አዲስ መዋቅር የትኞቹ መደቦች እንደሚገነቡትና እንዴት እንደሚገነቡት መግለጥ ነው::ይህ ካልተደረገ፣ ''አብዮት'' የሚለው መፈክር በአሁኑ ጊዜ ትርጉም አይኖረውም::'' /ሌኒን ቮል.9 ገጽ 128/

ዛሬም በአገራችን ይኸው ነው::የዚህን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የመደብ ይዘት በደንብ መግለጥ ያስፈልጋል::እንዴት እንደሚመጣም መግለጥ ያስፈልጋል::ይህ በትክክል ካልተደረገ፣ ማንም ተራማጅ ነኝ የሚል ሰው አውቆም ሆነ ሳያውቅ፣ ከአድሃሪያን ጋር መሰለፉ ግልጽ ነው::

በባሪያ ዘመን ''ህዝብ'' የሚለው ፈሊጥ የሚያመለክተው የባርያ ገዥዎችን መደብ ነበር:: በዚያን ጊዜ ለምሳሌ ግሪኮች ያቋቋሙ የነበረው ዲሞክራሲያዊ መንግስት ''ህዝባዊ'' ነኝ ቢልም የመምረጥና የመመረጥ መብት የነበራቸው ባርያ ገዥዎች ነበሩ::በፊውዳሉ ስርአት እነአሌ ሃይለስላሴ ''ህዝብ'' ሲሉ የመሳፍንቱንና የባላባቱን መደብ አባሎች ለመጥቀም ነበር::ዛሬም እነአስፋወሰን ህዝባዊ መንግስት ሲሉ፣እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ፣ የፊውዳሉን መደብ አባሎች ነው::በከበርቴ ስርአት ህዝባዊ መንግስት ሲባል ''ህዝብ'' ተብሎ የሚቆጠረው የከበርቴው መደብ ነው:: በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ባለው አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ደግሞ ህዝባዊ መንግስት ሲባል፣ ህዝብ የሚለው ክልል ውስጥ ወዝአደሩ፣ አርሶአደሩ፣ ንኡስ ከበርቴውና ሌሎችም ፀረፊውዳል ፀረኢምፔሪያሊስት የሆኑ ሃይሎች ሁሉ ይጠቃለላሉ::በተራማጅ ስም የሚፍለሉ የዲሞክራሲያ አድርባዮች በያዝነው ዘመን እውነተኛው ህዝባዊ መንግስት የመደብ ይዘቱ እንዲህ መሆኑን አይስቱትም::ስለዚህ እነዚህ መደቦች ተደራጅተውና ታጥቀው ጠላቶቻቸውን ሳይደመስሱ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' ተመራርጠን እናቋቁማለን ሲሉ ፣ ለጊዜው የተደራጀው ንኡስ ከበርቴ መደብ ብቻውን ስልጣን ይያዝ ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው::በንኡስ ከበርቴ ደንፊያቸ በኩል እንግዲህ ይህ መፈክር ሲወረወር ''ግፋ ቢል'' ንኡስ ከበርቴው ''ለጊዜው'' የኢትዮጵያ ''ህዝብ'' እኔ ልሁን ብሎ ለማቋቋም የሚታገለው የንኡስ ከበርቴ አምባገነንነት የሚፀድቅበት መንግስት ነው ማለት ነው::ይኸ ደግሞ ቢበዛ ''የጊዜያዊ'' ህዝብ መንግስት ይባል እንደሆን እንጂ የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የሚባልበት ምንም ፈሊጥ የለም::

ስለዚህ የኢትዮጵያ ተራማጆች የሚታገሉለት ህዝባዊ መንግስት በመደብ ይዘቱ የሰፊው ህዝብ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው::በአመጣጡ ደግሞ፣"በዲሞክራሲያዊ ምርጫ" ሳይሆን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን የሚደመስስ፣ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ አብዮታዊ አመጽን ይጠይቃል::የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ተጋድሎ የሚወጣውን ፈተናና ችግር ተወጥቶ አልፎ የሚሄድበት ጎዳና፣ በአድሃሪ ሃይሎች ላይ ወሳኝ ድልን ተጎናጽፎ የሚጓዝበት ጎዳና ይህ ብቻ ነው::

ዛሬ በኢትዮጵያ ይምጣ የሚባለው መንግስት ''ህዝባዊ መንግስት'' እንደሆነ ''ፀረጉግማንጉጌ'' ገስጋሽ ንቅናቄ ትስማማለች፤:አስፋወሰን/መንገሻም ይስማማሉ፤ የነሲአይኤ ፍጡሮች የሆኑት እነ''የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረትም'' ይስማማሉ፤ እነዲሞክራሲያም ይስማማሉ:: ሃቀኛ ተራማጆችም ትግላቸው ትንንቃቸው ለዚሁ ለህዝባዊ መንግስት ነው:: ነገር ግን ሃቀኛ ተራማጆች ይህ ህዝባዊ መንግስት ሊመጣ የሚችልበትን አብዮታዊ የትጥቅ ትግል ጎዳና ለጭቁኖች ባይታክቱ እያሳዩ መራራ ትግላቸውን ያካሂዳሉ::ከፀረጉግማንጉጌ ንቅናቄ አንስተን ''ወደገራ'' እየተጓዝን እስከ ንኡስ ከበርቴ ደንፊዎ እስከዲሞክራሲያ ድረስ ያለው የፀረህዝብና የፀረአብዮት ጥርቅም ደግሞ ለማወናበድና ሁሉም የበኩሉን የመደቡን ፀረህዝብ አምባገነን አገዛዝ ለማንገስ የሚመክረው ይህንን አብዮታዊ ጎዳና እያጭበረበረ ነው::

ዛሬ ይህ የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት መፈክር ይህንን አብዮታዊ የትግል ጎዳና ለማመልከት እስካልተገደዱ ድረስ የህዝቡን ትጥቅ ለማስፈታትና አብዮቱን ለመቀልበስ የሚዘጋጁ የጥፋት ሃይሎች ሁሉ የሚቀበሉትና የሚታገሉለት መፈክር ነው::

ሁሉም ይህንን መንግስት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ እናመጣዋለን ይላሉ፡፡ሁሉም የትግሉን መግፋት፣ የህዝቡን መደራጀትና መታጠቅ አጥብቀው ይፈራሉ፡፡እነኢሰፓወስን —መንግሽ ስዓም ይህንን አፍረጥርጠው ይናገራሉ፡፡የመንግሽ ስዓም የማርች 30 1974 መግለጫ ''ስልጣን ከምርጫ ሳጥን እንጂ ከጠመንጃ አፈሙዝ መውጣት የለበትም'' ያለው ይህንኑ የህዝቡን መታጠቅ የሚፈራ መደባዊ አቋሙን ሲያስተጋባ ነው፡፡የዲሞክራሲያ አድርባዮችም የትጥቁን ነገር ለማምለጥ የሚሞክሩት እሱን ችላ በማለትና የምርጫውን ነገር አጥብቀው በመያዝ ነው፡፡

የነሲአይኤና የነኢሰፓወስን የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት መፈክር ሌላ አላማው ነገሩ አለቀጥ ሳይዘገይ ህዝቡ ትጥቁን ፈትቶ ወደምርጫ እንዲሄድ ለማድረግ የተጠነሰሰ ሴራ ነው፡፡ህዝቡ በንቃቱ፣ በድርጅቱ፣ በትጥቁ እየገፋ ከሄደና እነሱ ተደቁሰው ካለቁ በኋላ ምርጫ ቢደረግ እውነትም ህዝባዊ ምርጫ እንደሚሆን ያውቃሉ፡፡ስለዚህ አላማቸው ትግሉ ሳይገፋ ለማቀዝቀዝ ነው፡፡ይህ ትግሉ ይብረድ የሚለው ቅዠታቸው ራሱ ለመንግስታቸው በሚሰጡት ስም ላይ ተለጥፎ ያጋልጣቸዋል፡፡የመንግሽ ስዓም የማርች 30 መግለጫ ይህንን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስቱን ''የብሄራዊ እርቅና የሃገር መገንባት ዲሞክራሲያዊ መንግስት''/ዲሞክራቲክ ገቨርንመንት ኦፍ ናሽናል ሪኮንስትራክሽን ኤንድ ሪኮንሲሊዬሽን/ ይለዋል፡፡መልእክቱ ግልጽ ነው፡፡ትግሉን ተውት፣ እንታረቅ፣ ነው የሚለው፡፡ የዲሞክራሲያ አድርባይ ምሁራንም በወፍ ቋንቋ አደበሰበሰው ያቀርቡት እንጂ ከአቀራረባቸው የህዝቡ ትግል እንኳን መታጠቁን ይቅርና በወጉ ስር ሰዶ መደራጀቱን ይፈራሉ፡፡በምርጫ ተውጣጥቶ ይቋቋም የሚሉት ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት የሚውጣጣው ''አሁን ካሉት፣ ከፈረሱትና፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊቋቋሙ ከሚችሉት ህዝባዊ ድርጅቶችና ... ፓርቲያች'' ነው ብለው እንመራረጥ ነው የሚሉት፡፡ እንዲያውም እስቲ ወደዚህ ወደጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው አመጣጥ ጉዳይ ጠለቅ ብለን እንግባ፡፡

መጀመሪያ ነገር የአድርባዮቹ ውዥንብር የሚጀምረው ገና ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' የሚለው ቃል ላይ ነው፡፡እነሌኒን ''ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት'' ሲሉና አድርባዮቹ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' ሲሉ በአብዮትና በፀረአብዮት፣ በብርሃንና በጨለማ፣ በጥራትና በውዥንብር መሃከል ያለው ልዩነት እንዳለ መመልከት ያስፈልጋል፡፡''ህዝባዊ'' መንግስት የሚባለው መላው ህዝብ ተሳትፎበት ከተካሄደ ነፃ፣ ምስጢርና ቀጥታ ከሆነ ጠቅላላ ምርጫ የሚወጣ መንግስት ለማለት ነው፡፡የሚገዛውም በፀደቁ፣ ባሉ፣ ሁሉ በሚያውቃቸው ህግጋትና የስልጣን ክፍፍሎች ላይ የተመረኮዘ የተረጋጋ መንግስት ለመጠቆም ነው፡፡አብዮታዊ መንግስት ግን በጠቅላላ ምርጫ ሳይሆን፣ በአብዮታዊ ትግል በደመሰሰው መንግስት ተተክቶ፣ በቆዩና በተደነገጉ በተረጋጉ ህግጋትና የስልጣን ክፍፍሎች ላይ ሳይሆን ለትግሉ መግፋትና ለፀረአብዮት ሃይሎች መደምሰስ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ እየወሰደ፣ አዲስ ስርአት መልክ ባለው ሁኔታ እስኪቋቋም ድረስ የሚሰራ የመሸጋገሪያ መንግስት ነው፡፡እንዲህ አይነቱ ስልጣን በአብዮቱ አፍላ ጊዜ የሚቋቋምና በሌኒን አነጋገር ''ምንም ሌላ ስልጣን የማያውቅ፣ ያወጣ ባለስልጣን ቢያወጣቸው ምንም ህግጋት፣ ምንም ደንቦችና ወጐች የማያዙት፣ ወሰን የሌለው፣ ከህግ ውጭ የሆነና በቀጥታ በሃይል ላይ የተመሰረተ'' መንግስት ማለት ነው፡፡

እንዲያውም እነሌኒን እንዲህ አይነቱን ''ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት'' የጠየቁት ዝቅ ብለን እንደምናየው፣ አንዱ አላማው ጠቅላላ ምርጫው በመላው ህዝብ፣ በቀጥታ፣ በሙሉ ነፃነትና በምስጢር ለማስደረግና ህዝባዊ ሪፐብሊክን የሚያቋቁም ባለሙሉ ስልጣን የእንደራሴያች ሸንጎ ለማስመረጥ ነው፡፡በነሌኒን እምነት ይህ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ሊቋቋምና ነፃ ምርጫውን ሊያካሂድ የሚችለው በፀረህዝብ ሃይሎች ላይ የተሳካ ህዝባዊ አመጽ አድርጎ ስልጣን ሲጨብጥ ብቻ ነው፡፡ ጀግኖቹ የቪየትናም አርበኞችም በትግል ውስጥ ባሉበት ጊዜ ብዙ ግዛቶችን ከቁጥጥራቸው ስር ካደረጉ በኋላ በምርጫ ሳይሆን በአብዮታዊ አመፃቸው ላይ ተመርኩዘው ያቋቋሙት መንግስት ጊዜያዊ አብዮታዊ እንጂ ጊዜያዊ ህዝባዊ ያልተባለው ለዚህ ነው፡፡

እንግዲህ አንድ ህዝባዊ መንግስት ጊዜያዊ ይባል ቋሚ ከመላው ህዝብ ምርጫ የሚፈልቅ መንግስት ነው፡፡አብዮቱ ተሳክቶ ፀረህዝብ ሃይሎች ተደምስሰው፣ ወይም ከቁጥጥር ስር ውለው ነፃ ምርጫ ተደረገ እንበል፡፡ይህ ከሆነ ከዚህ ነፃ ምርጫ የሚወጣው መንግስት በርግጥም ህዝባዊ የሆነ መንግስት ለምን ጊዜያዊ እንደሚባል ጠርጦ ምስጢረሰሳሱ ይሆንብናል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ፀረአብዮት ሃይሎች አይለው ህዝቡ በሙሉ ነፃነት ምርጫውን እንዲያካሂድ ከከለከሉት፣ ወይም አድሃሪ ተ

ተጽእኖዎቻቸውን ካሳደረባት ይህ ''ጊዜያዊ'' ጉድ በምን ፈሊጥ ''ህዝባዊ'' ሊባል እንደሚችል አሁንም ከምስጢረስላሴ የረቀቀ ምስጢር ይሆንብናል::ባጭሩ አድርባዮቹ እናመጣዋለን የሚሉት መንግስት በርግጥ ህዝባዊ ከሆነ ጊዜያዊ መሆኑ አይታየንም::''ህዝባዊ''ካልሆነ ደግሞ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች በትግላቸው ገፍተው ነፃ ይወጣሉ እንጂ ''ለጊዜውም'' ቢሆን የምትጭኑባቸውን ባርነት አይቀበሉም::''ጊዜያዊ'' እና ''ህዝባዊ'' አንድ ላይ የሚሄዱ ነገሮች አይደሉም:: እሳትና ጭድ ናቸው::ብቻ ገና ስንት የተደገሰለትን አንባቢ በእንደዚህ አይነቱ ''ፀጉር መሰንጠቅ'' እናድክመውና ወደሌላ እንቀጥል::

የዴሞክራሲያ አዘጋጆች በዚህ ጉዳይ ላይ ከነአስፋወሰንና ከነመንገሻ ስዩም ጋር ቆመው ሲያራግቡ የሚያዙት ስለዚህ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው'' መተቸት ሲጀምሩ ነው::በነሱ ግምት የዚህ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' አመጣጥና ቀደም ተከተል እንደሚከተለው ነው::

- ''ለሃቀኛ አብዮታውያን የትግል መሳሪያ የሆኑት የመሰብሰብ፣ የመናገር፣የመፃፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመደራጀት ሰብአዊ መብቶች ያለምንም ገደብ መልቀቅ፣
- ''አሁን ካሉት፣ ከፈረሱትና በአጭር ጊዜ ለመቋቋም ከሚችሉት ህዝባዊ ድርጅቶችና/የገበሬ ማህበራት፣ የንኡስ ከበርቴ የሙያ ማህበራት፣ የሴቶች ማህበራት፣ የሰራተኛ ማህበራት፣ የመምህራን ማህበራት፣ ሰፊው ወታደር.../ ፓርቲያች በምርጫ የሚወጣጣ ጊዜያዊ ህዝባዊ ሸንጎ ማቋቋም፣
- ''በዚህም ጊዜያዊ ህዝባዊ ሸንጎ የሚመረጥ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት መመስረት ያስፈልጋል::''

ለምን እንደዚህ በኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች እንባና መከራ ታላግጣላችሁ? አሁን ማን ይሙት የኢትዮጵያ ጭቁኖች ''በነፃ'' ስለተናገሩ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ስላደረጉ ...ብቻ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በንግግርና በሰላማዊ ሰልፍ ብርታት ተንኮታኩተው ይወድቃ መስሎአችሁ ይሆን? የኢትዮጵያን ህዝቦች ጥያቄ በዚህ ብቻ አስከወሰናችሁት ድረስ እነሲአይኤም አብረዋችሁ ይሰለፋሉ::ይህንንማ እነአስፋወሰን –መንገሻም እስከነስሙ ''የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት'' ብለው በሰየሙት ድርጅታቸው ፕሮግራም ላይ በሙሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ''ጠይቀውለታል''::ነገር ግን የኢትዮጵያ ጭቁኖች በነዚህ መብቶች ላይ በተጨማሪ፣ የነአስፋወሰን –መንገሻን፣ የኢምፔሪያሊስቶችን አመጽ ለመመከት፣ በገዛ አገራቸው በሰላም ለመስራትና ለመኖር እንዳይችሉ ከታወጀባቸው የርስ በርስ ጦርነት በድል አድራጊነት ለመውጣት የመታጠቅ መብታቸውን ይጠይቃሉ::ይህማ ከሌለ ያየነው ነው::ሚሊዮን የመጋር መብት ቢኖራቸው፣ ባዶ እጃቸውን እስከሆኑ ድረስ የታጠቀ አድሃሪ አያናግራቸውም::ሚሊዮን የመደራጀት መብት ቢታወቅላቸው የታጠቀ አድሃሪ ይበትናቸዋል::ዛሬ አብዮታዊ ዘማቾች በጥይት እየተቆሉ፣ በእሳት እየተጠበሱ መስዋእትነትን ተጋፍጠው በመታገል ላይ ናቸው::ድሃ ገበሬዎችና የመሬት ይዞታ ሰራተኞች የአድሃሪያች ጥይት ራት እየሆኑ በመተናነቅ ላይ ናቸው::ይህ ሁሉ የሚወርድባቸው የአድሃሪያች አመጽ እስከዚህም የመደራጀት መብት በመነፈጉ ሳይሆን፣ በፀረ ዲሞክራቲኩ የደርግ አገዛዝ የመታጠቅ መብቱን በመነፈጉ ነው::ይህ አልገባችሁ እንደሆነ ስለኢትዮጵያ አብዮት የገባችሁ ሳንቲም ነገር የለም ማለት ነው::

አድርባዮቹ የጭቁን ህዝቦችን መታጠቅ በጣም ይፈራሉ::ስለዚህ ይህንን ሳያነሱ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል ለመጠቆም ሲሞክሩ ጨርሰው ትርምስ ውስጥ ነው የሚገቡት::

በመጀመሪያ ነገር ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸውን ከነሌኒን ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ጋር የግድ ለማዛመድ ቢሞክሩም የአድርባዮቹ መንግስት አቋቋም ቀደም ተከተል ሲታይ ከአብዮታዊ ጊዜያዊ መንግስት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ግልጽ ይሆናል::እንደዴሞክራሲያ አባባል ከሆነ በመጀመሪያ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ ሸንጎ'' ከምርጫ ይውጣጣና ከዚያ በኋላ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ይመረጣል::በጠም ጥሩ! የነሌኒን ደግሞ የተገላቢጦሽ ነው! የእነሱ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ከምርጫ ተውጣጥቶ ሳይሆን ከተካካ ህዝባዊ አመጽ ይወለዳል::ከዚያ በኋላ ጠቀለለው ህዝብ ነፃ፣ ቀጥታና ምስጢር በሆነ ምርጫ ተሳትፎ ህዝባዊ የመማከርት ሸንጎ ያቋቁማል::ይህ ባለሙሉ ስልጣን የሆነ የህዝብ እንደራሴያች ሸንጎ ህዝባዊ መንግስት ያቋቁማል::

የተጥቀን ነገር ፈጽሞ አረሳስታቸሁ፣ በምርጫ እናመጣዋለን የምትሉት መንግስት እንኳን ከነሌኒን አብዮታዊ መንግስት ጋር አንድ ሊሆን ይቅርና የሱ ተቃራኒ እንደሆነ ግልጽ ነው::አድርባዮቹ ግን ይህን አድሃሪ መፈክራቸውን በገናናያቹ በነሌኒን ስም ሸፋፍነው ለማሳለፍ "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን ጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ታሪካዊ ሃቆች አሉን"/?/ በሚል አርእስት ስር የሩስያን ቦልሼቪኮች ታሪክ ምሳሌነት እየጠሩ ይተነትናሉ::የዲሞክራሲያን ቁጥር 24 ይህንን የመጨረሻ ክፍል ስናይ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ገና ለረጅም ጊዜ <u>ሲያስፍረን</u> የሚኖረውን የክርክርና የአጠቃቀስ ዘዴ ታዘብን አዘንን::ይህንን ዝቅ ብለን እንመጣበታለን::

በዚህ በጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በቦልሼቪኮችና በሜንሼቪኮች መሃከል ብዙ ሌሎች ልዩነቶች ነበሩ::በጠቅላላው ግን የልዩነታቸው መሰረት እነሌኒንና አድርባዮቹ ስለጠቅላላው የሩስያ አብዮት የተለያየ አስተሳሰብ ስለነበራቸው ነው::በ1905 ዓ.ም. የንጉሱ አገዛዝ በህዝብ ትግል ተወጥሮ ተይዞ ባለ እየተጋጋለ የሚሄደው አብዮት እንዴት እንደሚገፋ በተደረገው ውይይት ሁለቱ ቡድኖች የተለያየ ታክቲክ ለመከተል ወሰኑ::

እነሌኒን ይህ አብዮት፣ ምንም እንኳን የከበርቴ አብዮት ቢሆን ቅሉ፣ ከበርቴው እጅግ ወላዋይ በመሆኑ ከንጉሱ ጋር ተዋውሎ አንድ አይነት ቀይጥ መንግስት ያመጣ እንደሆን እንጂ፣ በእርግጥ ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክን ሊያመጣ አይችልም::ይህንን ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ ለማምጣት የሚችለው ወዝአደሩ ከአርሶአደሩ ጋር ተባብሮ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ ዲሞክራሲያዊ የወዝአደርና የገበሬ መንግስት ለመመስረት በመሪነት ሲታገል ነው እያሉ ይከራከሩ ነበር::ይህንንም የወዝአደርና አርሶአደር አምባገነን መንግስት፣ ይህንን ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ ለማቋቋም አንድ ባለሙሉ ስልጣን የሆነ የህዝብ እንደራሲያች ሸንጎ ማስመረጥ ያስፈልጋል::ይህ ሸንጎ በርግጥ ባለሙሉ ስልጣን እንዲሆን፣ በርግጥ የህዝብ እንደራሲያች ሸንጎ እንዲሆን ከተፈለገ ይህንን ምርጫ ሊያካሂድ የሚችለው <u>በተሳካ ህዝባዊ አመጽ አድሃሪያችን ደምስሶ የሚቋቋም ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ብቻ</u> እንደሆነ እነሌኒን ደግመው ደጋግመው ያስረዱ ነበር::

አድርባዮቹ ሜንሼቪኮችስ? ሜንሼቪኮች ይህ አብዮት የከበርቴ አብዮት እንደመሆኑ መጠን ሊመራው የሚችለው ለዘብተኛው /ሊበራሉ/ ከበርቴ እንጂ ወዝአደሩ አመራለሁ ብሎ ከበርቴውን ማስደንገጥ የለበትም ይሉ ነበር::ከዚህም አልፎ ተርፎ ወዝአደሩ ከገበሬው ጋር አንድነቱን ማጠንከሩን ትቶ ተብብሩን ከዚህ ከለዘብተኛው ከበርቴ ጋር ያድርግና ንጉሱን ለመጣል በሚያደርገው ትግል ይርዳው ይሉ ነበር::ከበርቴው "ተደናግጦ አብዮቱን እንዳይተወው" ወዝአደሩ የዚህን መንግስት እንኳን አመራሩን ይቅርና ተሳትፎ እንኳን መጠየቅ የለበትም የሚል አቋም ነበራቸው::የንጉሱን አገዛዝም ለመደምሰስ እንግዲህ እነሌኒን የትጥቅ ትግልና እሱ ሲሳካ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት፣ ከዚያም ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሲሉ አድርባዮቹ <u>ወይ</u> የተሳካ ህዝባዊ አመጽ ተደርጉ <u>ወይም</u> ደግሞ ህዝቡ የእንደራሲያች ሸንጉ እንዲጠራ አስጨንቆ ይዞ ምርጫ እንዲደረግ ቢያስወስን ወሳኝ የሆነ ድል /ዲሳይሲቭ ቪክትሪ/ ይገኛል ብለው ይፃፉ ነበር::

ሌኒን ይህ ድል ሊገኝ የሚችለው ከተሳካ ህዝባዊ አመጽ ብቻ ሊወጣ በሚችለው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ብቻ እንደሆነና ፀረህዝብ ሃይሎች ሳይደመሰሱ ወይም ሳይዳከሙ ምርጫ ቢደረግ በምንም አይነት እንደድል ሊቆጠር እንደማይቻል ሲያስረዳ የሶስተኛውን የፓርቲውን ጉባኤ ውሳኔ እየተቸ እንዲህ ይላል::

"የጉባኤው ውሳኔ እንደሚያመለክተው የቅስቀሳ ሙሉ ነፃነትን አረጋግጦ፣ በእውነት የህዝቡን ፍላጐት ለማንፀባረቅ የሚችል ባለሙሉ ስልጣን የእንደራሲያች ሸንጐ ለማስመረጥ የሚችለው፣ የተሳካ ህዝባዊ አመጽ መሳሪያ የሆነው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት <u>ብቻ</u> ነው::ይህ አስተሳሰብ ትክክል ነው ወይ? እቃወማለሁ የሚል ካለ የንጉሱ መንግስት ለአድሃሪያች እጁን ሳይዘረጋ ይችላል፣ በምርጫው ውስጥ ገለልተኛ መሆን ይችላል፣ ህዝቡ በእውነት ፍላጐቱን እንዲገልጽ ይፈልጋል ብሎ መከራከር ይኖርበታል::እነዚህ አስተሳሰቦች እጅግ አስቂኝ ከመሆናቸው የተነሳ /አድርባዮች እዳምጡት ሌኒንን! ሰ.ህ.ዶ./ ማንም ቢሆን በግልጽ ሊቀምላቸው አይችልም::"

በነገራችን ላይ አድርባዮቹ /የኛን ማለታችን ነው/ ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው ምን አይነት ድል እንደሆነ ራሳቸው እርግጠኞች አይደሉም::ስለዚህ መንግስት ምንነት ብዙ ከተናገሩ በሗላ ገጽ 5 ላይ ይህ የፊውዳሊስቶቹና የነሲአይኤ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት በምርጫ ተውጣጥቶ ቢቋቋምም የተገኘው የውሸት ድል ፀረህዝብ ድል እንጂ ሌላ ምንም ነገር እንዳይደለ ሲያምኑልን ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ''ወደ ሃቀኛ ህዝባዊ ድልም የሚመራ የተግል መሳሪያም ነው'' ብለውን ቁጭ ይላሉ::ብቻ ይህንን እንተወውና ወደሌላው ''ትንተናቸው'' ገብተን እንቃከር::

እንግዲህ የነሌኒንና የሜንሼቪኮቹ ልዩነት ባጭሩ በነዚህ ነጥቦች ላይ ነበር::ከላይ ስንጽፍ በዚህ ጉዳይ ላይ የኛ አድርባዮች እነሌኒንም እንደኛው በምርጫ የተውጣጣ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ነበር የሚጠይቁት፣ እኛ በተነሳው ክርክር በቦልሼቪኮች በኩል ነበርን፣ ታሪክ ይደግፈናል ለማለት ያቀረቡትን ጥቅስና የሰሩትን ማጭበርበር ስናይ ለኢትዮጵያ ተራማጆች አፈርን ብለነው ነበር::ለአንባቢም ጉዱን እናሳየውና ሃፍረት አይሰማው እንደሁ እንይ::

ስለአብዮታዊ አመጽ፣ ስለሚቋቋመው የመንግስት አይነት /የመደብ ይዘት/፣ ስለነበረት ልዩነቶች ሳንቲም ሳያወሩ፣ ቃል ሳይተነፍሱ ''በዛሩ መንግስት ቦታ ስለሚቋቋመው/!?/ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ላብአደሩም ስለሚኖረው ተሳትፎ ማርክሲስቶቹ ቦልሼቪኮችና አድርባዮቹ ሜንሼቪኮች የተለያዩ አቋሞች ወስደው ነበር'' ይሉናል::እንኳን የልዩነቱን ታሪክ በሚገባ የሚያውቅ ሰው ይቅርና ከላይ የሰጠነውን ትንተና የተመለከተ አንባቢ ''እንዴት በዚህ ብቻ ነው ልዩነቱ?'' ብሎ መገረም ይጀምራል::ከዚያ ''የቦልሼቪኮቹ መሪ የነበረው ሌኒን፣ ሁኔታውን እንደሚቀጥለው በመመልከት'' ይሉና ሌኒንን የጠቀሱ መስለው እንደሚከተለው ይጽፋሉ::

> ''... የሚቋቋመው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት ተግባር የአብዮቱን ድል ማጠናከር፣ ፀረአብዮታዊ እንቅስቃሴውን መደምሰስና የሶሻልዲሞክራቲኩን ሌበር ፓርቲ ዝቅተኛ ፕሮግራም በስራ ላይ ማዋል ይሆናል::እነዚህ ተግባራት ካልተከናወኑ በስተቀር በዛሩ ላይ የተሟላ ድል ሊገኝ አይቻልም::እነዚህን ተግባራት በስራ ለማዋልና በዛሩ ላይ ሙሉ ድል ለመቀዳጀት ደግሞ ጊዜያዊው አብዮታዊ መንግስት እንደማንኛውም ተራ አይነት መንግስት ሳይሆን የላብአደሩና የአፈርገፊው አምባገነን መንግስት መሆን አለበት::..... ላብአደሩ በጊዜያዊው አብዮታዊ መንግስት ተሳትፎ አብዮቱን መምራት አለበት::እ...

አንዱ የመጀመሪያ ነገር::እዚህ ላይ አድርባዮቹ ሌኒንን አሳይተው የሚጠቅሱት ስታሊንን ነው::ሌኒን እነዚህን አሳቦች አልሰነዘረም ለማለት አይደለም እዚህ ላይ ፀጉር እንሰንጥቅ የምንለው::አድርባዮቹ ነገሩ እንዲህ በመጉማመዱ አንባቢ ድንገት ግራ ተጋብቶ እስኪ ላጣራ ቢል እንዳይጋለጡ አስበው ነው ይህንን የጠቀሱት ከስታሊን ''ሂስትሪ ኦፍ ዘ ኮሙኒስት ፓርቲ ኦፍ ዘ ሶቭየት ዩኒየን'' ከተባለው መጽሃፍ ገጽ 64 እንደሆነ የሸሸጉን::ይብላን ለአወናባጆቹ እኛስ ደረስንበት!!

የነሌኒንን ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት አድርባዮቹ እናቋቁም ከሚሉት፣ በምርጫ አውጣጥተን እናምጣ ከሚሉት መንግስት ጋር አንድ ለማመሳሰል የሚቻልበት ጥቅስ አይደለም::የነሌኒንን የነስታሊንን አስተሳሰብ አረፍተነገሮቹን እየጎመዱ ለማጣመም ካልሞከረ በስተቀር ቃላትን ሳይቀር ከጀመሩ በሗላ እየተደናገጡ አርገፍ አድርጉ ካልተተወ በስተቀር::የጠቀሱት ጥቅስ ላይ ''የሚቋቋመው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት'' ከሚለው አረፍተነገር በፊት ሌላ የሸሸጉን አረፍተነገር አለ:: እሱውም የሚለው እንደሚከተለው ነው::

> ''ሌኒን ከተሳካ ህዝባዊ አመጽ በሗላ የዛሩ መንግስት በጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት መተካት አለበት እያለ ይከራከር ነበር::የሚቋቋመው ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት...''እያለ ነው ስታሊን የሚቀጥለው::ከዚያ አድርባዮቹ ''ይህ መንግስት... የላብአደሩና የአፈር ገፊው አምባገነን መንግስት መሆን አለበት::'' ብለው አረፍተነገሩ ሳያልቅ ጨለማ ውስጥ ጥለው ሲለዩን ስታሊን ''የወዝአደሩና የአርሶአደሩ አብዮታዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መሆን አለበት'' ብሎ እቅጩን ይነግረናል::

አድርባዮቹ ከዚህ አልፈው ''ወደ ተሳትፎ'' ጥቅሳቸው የሚሄዱት ገጽ ዘለው ነው::ግን ስታሊን ስለዚህ መንግስት አምባገነንነትና አብዮታዊነት ምን አውርቶ ነው አወናባጆቹ ነጥብ ነጥብ አድርገው ያለፉት? ያቺ ''እ...'' ብለው የጀመሯት ቃል ምን ትሆን? ይቺን ለመረዳትና አንባቢ በነዚህ አድርባዮች አንጀቱ እንዲቆርጥ ስታሊን ከዚህ አስከትሎ የዚህን በዛሩ ላይ የሚገኝ

የተሟላ ድል ይዞት የዚህን ጊዜያዊ መንግስት አብዮታዊነት ለማስረዳት ሌኒንን ይጠቅሱና ይህ አድርባዮች ሊያነሳሱን የፈለጉትን ከጦር የሚፈሩትን የትጥቅ ጉዳይ ቁልጭ አድርጉ ያመጡንቸውና ጠርሶ ያጋልጣቸዋል:: በኛ ግምት ''አ..'' ብለው የጀመሩትን ተጉርዳ የቀረቸው ጥቀስ እነሆ:-

''እንደዚህ አይነቱ ድል ደግሞ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንጂ ሌላ አይደለም:: ይህም ማለት የግድ በጦር ሃይል ላይ፣ በሰፊው ህዝብ መታጠቅ ላይ የሚመሰረት: አገዛዝ እንጂ በዚህ ወይም በዚያ አይነት በህግ በታወቁ፣ በሰላማዊ መንገድ በተቋቋሙ ድርጅቶች /ኢንስቲትሽንስ/ ላይ የሚመረኮዝ አገዛዝ አይደለም:: የግድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መሆን አለበት::ምክንያቱም ለወዝአደሩ፣ ለአርሶአደሩ በአስቸኳይና በግድ የሚያስፈልጓቸው ለውጦች የመሬት ከበርቴዎች፣ የከፍተኛ ቡርዥዋ መደብና የንጉሳዊው አገዛዝ ተቃውሞ ያጋጥማቸዋል::''

ግልጽ ነው::ወንድሞቻችን የቀሙሉት ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' እነሱ እንደሚሉት ''በታሪካዊ ሃቅ'' አልተደገፈችም::''ታሪካዊ ሃቅ'' የሚመሰከረው ጉዳይ ቢኖር 1ኛ/ ወንድሞቻችን ከቦልሸቪኮች ጋር እንዳልሆኑ፣ 2ኛ/ ሜንሼቪኮች እንኳን ከአቶማቸው አጥብቀው አይያዙት እንጂ የትጥቅን ጉዳይ አልፎ አልፎ ጠይቀዋል:: ነገር ግን ድል የሚገኘው ''ወይ በትጥቅ ትግል ወይ በምርጫ'' በሚለው ፈሊጣቸው ''በወዝአደሩ ህሊና ውዥንብር ይነዛሉ'' ብሎ ሌኒን ተቃውሟቸው ነበር::በዲሞክራሲያ አስተሳሰብ ግን ምንም ውዥንብር የለም:: የድል ጉዳና ብላችሁ የምታሳዩት የቀድሞ—አብዮት ሩስያ ለዘብተኛ ከበርቴን የምርጫ መንገዱ ብቻ፣ የነአስፋወሰን /መንገሻን የምርጫ መንገዱ <u>ብቻ</u> ስለሆነ አስተሳሰባችሁ አድሃሪ ጥራት አለው::እንደዚህም በመሆኑ የዲሞክራሲያ አዘጋጆች ሚልዮን ጊዜ ተንጠራሩ እንጂ አሰላለፋችሁ እንኳን ከቦልሸቪኮች ጋር ሊሆን ይቅርና ከሩስያ ሜንሼቪኮች <u>በስተቀኝ</u> እንደነበረና በዚያን ጊዜ እንደእናንተው የትጥቅን ጉዳይ ሳያነሱ ምርጫ ይደረግ ከሚሉት ከሩስያ መሳፍንት ጉን እንደሆነ ግልጽ ነው::

''የለም ቀይ! የኛ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ከምርጫ የተውጣጣ ነው ስለን እንጂ የነአስፋወሰን/ መንገሻ መንግስት አይደለም::እንዲያውም እነሱን የሚቃወምና እነሱም የሚቃወሙት መንግስት ነው!'' እያሉ አድርባዮች ከወንበራቸው ብድግ ሲሉ ይታዩናል::መውጪ ቀዳዳ የተገኘ መስሎአቸው ይሆን ዲሞክራሲያ ቁጥር 24 ''የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተቃዋሚያች እነማን ናቸው'' በሚል የተቸቸውን ጠቋሙን ለማምለጥ ይሞክራሉ::እውነትም ለጠላት ስም የሚሰጠውን ዝርዝር የተመለከተና፣ ያበጠበጡትን የምርጫ ተስፋ የሙጥኝ ብሎ ያነቀ የዋህ ይህንን ሊስት ሲመለከት ጠርሶ ሊደናገጥ ይችላል::አብዮታውያን ግን ይህንን ሊስት ሲመለከቱ የዲሞክራሲያን አዘጋጆችና የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸውን <u>ማንነትና</u>፣ በሊበራል ከበርቴ ቅዠት ተውጦ የሚዋዥቀውን የፖለቲካ መስመራቸውን ኪሳራ ጥልቀት ከመቼውም ይበልጥ ይረዱና ይቆርጥላቸዋል::እንደዲሞክራሲያ አባባል:-

''የዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተቃዋሚያች እነማን ናቸው?

''በመጀመሪያ ደረጃ፣ ስልጣን የጠማውና በህዝቡ ብሶትና ጭንቀት ተንሰራፍቶ ለመቀየት የሚፍጨረጨረው የምርጥ መኮንኖች መንግስት የዚህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አይነተኛ ተቃዋሚ ነው::

''በየቦታው ህዝቡን እያወናበዱ እንደገና የፊውዳሉ ስርአት ትንሳኤ እንዲያደርግ የሚጥሩት መሳፍንቶችና ባላባቶችም የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተፃራሪያች ናቸው::

''የህዝባዊ መንግስት መቋቋም የበዝበዛ ጥቅሞታቸውን የሚሰባብርባቸው የቢሮ ከበርቴዎችና አቀባባይ ከበርቴዎች የጊዜያዊ ህዝባዊውን መንግስት መቋቋም ለማክሸፍ አይመለሱም::

''በተራማጅ ለምድ ተሸፋፍነው የህዝቡን አብዮታዊ የትግል ግለት ለማቀዝቀዝና አቅጣጫውን ለማስቀየር የሚቅርዘበዙት ሶሻልሾቪኒስቶችና ሶሻልፋሽስቶች ሌሎችም የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጸሮ ተቃዋሚያች ናቸው::

''የሃገሪቱን የስራ ጉልበትና ጥሬ ሃብት በርካሽ ዋጋ እያንጋፈፉ በሌላ በኩል የፋብሪካ ያቻቸውን ግስንግስ በአጥፍ ድርብ ዋጋ እያራገፉ ህዝቡን የሚበዘብዙትና የሚያለቡት አለምአቀፍ-ባለወረቶች ጊዜያዊው ህዝባዊ መንግስት እነዚህን የትርፍ ትርፍ ምንጮቻቸውን ስለሚደፍንባቸው መቋቋሙን አጥብቀው ይቃወማሉ:: ከነስልጣን ላይ ካለው የምርጥ መኮንኖች አቀባባይ ከበርቴዎችም ጋር በመመሳጠር ልዩ ልዩ ወጥመዶች ይዘረጋሉ::''

ምስኪን <u>ዲሞክራሲያ</u>! የነ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ተቃዋሚው ብዙ ነው ብላ ጠላቶችዋን እንደአሸዋ እየቆለለች ስትደነፋ፣ <u>በዚህ ብቻ</u> ይህ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትዋ <u>አብዮታውያን እን</u>

ባለው ''የሕዝብ ዲሞክራሲ'' መንግሥትና ወታደራዊ ፋሽስት አገዛዝ ውስጥ ሰላም ሊሰፍን አይችልም። ህዝቡ እንደሚጠብቀው ''ከምርጫ በማውጣጣት'' ለማቋቋም እን
ደሚሉት በታጠቀ ህዝባዊ አመጽ አንጂ አሷ አንደምትለው ''ከምርጫ በማውጣጣት'' ለማቋቋም እን
ደማይቻል ወለል አድርጋ አምናለን ራሷን በጥፊ መታቸና ቆሞ አለች::

እዚህ ላይ መቼስ ቢያንስ ቢያንስ ተራ ሊበራል ከበርቴ አንደሆናቸሁ ብታምኑለን ይሻላች ሂል::አለበለዚያ የባሰ ጉድ ነው::

መቼም አንድ ሰው አድርባይም ሆኖ ተራ ሉኚክ ሊገባው ይቸላልና እናንተም የሚከተለውን ልብ አንድትሉ አንጠይቃቸሂለን::ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታችን አነዚህ ሁሉ ጠላቶች አሉበት ስትሉ ''አይነተኛ ተቃዋሚው'' ''ጸኑ ተቃዋሚው'' ''የዚህን መንግስት መቋቋም ለማከሸፍ የማይመለሰው'' ''ተፈራሪው'' አለፍ ተርፎም ይህ ሁሉ የፀረህዝብ ጥርቅም ''እየተመሳጠረ ልዩ ልዩ ወጥመዶችን እየዘረጋ'' ያስቸግራል ስትሉ ይህንን መንግስት ለማቋቋም ሃይለኛ ተጋድሉ አንደሚያስፈልግ ታምናላቸሁ ማለት ነው::ይህን ሁሉ ተቃውሞ ማሸነፍ አለበት ማለት ነው::ለዚህም የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች የረዥም ጊዜ የተወሳሰበ የፖለቲካና የጦር ትግል አያስፈልጋቸውም ትሉ እንደሆነ፣ በምርጫ በመውጣጣታቸን ብቻ ተደናግጠው የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠላቶች ከታሪክ መድረክ ይወርዳሉ ትሉ እንደሆነ መቼስ ከሊበራል ከበርቴ ቅዠታቸሁ አንድትነቁ ከመፀለይ ሌላ የምናደርግላቸሁ ነገር የለም::ግን ከፍ ብለን እንዳልነው ይህንን ብታምኑለን ይሻላል::አለበለዚያማ አሳማቸን ከነዚህ ''እንመራረጥ'' ከሚሉ ፊውዳሊስቶቸና አቀባባዮች ሁሉ ጋር ሆነን፣ ፀረደርግ የሆነ ''ዲሞክራሲያዊ'' መንግስት ለማቋቋም ነው የሚል ጨርሶ አድሃሪ የሆነ አቋም ወስዳቸሁ መጋለጥ ይሆንባቸሂል:: ነው ወይስ አቋማቸሁ ይሽ ይሆን? እስቲ አንባቢ ይህንን የጠላቶች ዝርዝር አንደገና ይመልከተውና እኛ የታዘብነውን ሌላ ጉድ ይታዘብ!

''በመጀመሪያ ደረጃ'' የዚህ መንግስታቸው ''አይነተኛ'' ተቃዋሚ ደርጉ መሆኑን ይነግሩናል::ታዲያ በዚህ የሚያሳዩን ምንድነው? በዚህ ቅደም ተከተላቸው የሚያምኑለን ይህ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስታቸው'' ''በመጀመሪያ ደረጃ ፀረደርግ መፈክር መሆኑን ነው::በዚህ ጥቅሳቸው ከምርጫ የሚወጣው ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት መፈክር እንዳልሆነ ማመናቸውን አድርባዮቹ ጨርሶ ልብ አላሉትም::የአስፋወሰን/መንገሻ ዴሞክራቲክ ህብረት ንቅናቄ ጊዜያዊ መንግስት የጠየቀው ባስቸኳይ ''የማይገባውን ስልጣን እጁ ያስገባውን፣ አገሪቱን በፋሽስታዊ አመጽ ጨብጦ የያዘውን ፋሽስታዊ ደርግ'' ለመጣል እንደሆነ በኦክቶበር 8 ቀን መግለጫው አስታውቋል::አድርባዮቹ ደግሞ ይህንን መንግስት የሚጠይቁት ''ራሱን የቻለ የመንግስት ስርአት ሳይሆን እየተጠናከረ የሚሄደውን ወታደራዊ የፋሽስት መንግስት በአጭር ለመቅጨት...'' እንደሆነ ሲያስታውቁን ቀጥታ ከፊውዳሊስቶቹና ከነኢሕአሴ ጋር መቆማቸውን አለተረዱት እንደሆነ በኢትዮጵያ አብዮት፣ በ1968 ዓ.ም. ያለው የመደቦች አሰላለፍ ጨርሶ አልገባቸውም ማለት ነው::

እኛ ግን የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የመደቦች አሰላለፍ ጠንቅቆ ገብቶናል::ዋና ጠላቶቻቸን ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸው::የምንታገለለትና የምንሰዋለት ጊዜያዊ መንግስት ቢኖር በነሱ መቃብር ላይ በህዝባዊ አመጽ ተጠንስሶ፣ በህዝባዊ አመጽ ተመርኩዞ የሚገዛው የጭቁን ህዝቦች ፊላጭ ቀራጭ አብዮታዊ መንግስት ብቻ ነው::

ለዚህም የምንከተለውን ጉዳና ''አብዮቱ አንዲገፋ'' በሚል ትንተናቸን /ሰ.ህ.ድ. ቁጥር 25/ ገልጥለጥ አድርገን አሳይተናል::በመጀመሪያ ''መሬት ላራሹ'' በሚለው አብዮታዊ መፈክር ስር የተሰለፉት የኢትዮጵያ ገበሬዎቸ መሬትን እጃቸው ለማስገባት አስፈላጊ ሆኖ ሳገኙት ለነፃነታቸው ከፀረህዝብ ሃይሎች ጋር የሞት ወይም የሽረት ትንንቅ በማድረግ ላይ ናቸው::መሬትን እጃቸው ለማስገባት ከፈለጉ በየደረጃው ፖሊሱን፣ ዳኛውን፣ አስተዳዳሪውን፣ ባጭሩ የቀደሞውን ስርአት የመንግስት አውታሮቸ አየደመሰሱ ስልጣንን እጃቸው ማስገባት እንዳለባቸው ከገዛ አለታዊ ትግላቸው ተምረዋል::ለዚህም ተገባርና መሳፍንቱና ኢምፔሪያሊስቶቸ ያወጡባቸውን የርስ በርስ ጦርነት ለመመከት ''አስታጥቁን'' እያሉ በመጮህ ላይ ናቸው::ፀረዲሞክራቲኩ የደርግ አገዛዝ ''ማስታጠቅ ማጨረስ ነው'' በሚል ፈሊጥ የህዝቡን ጥያቄ አፍኖ ለመያዝ በመሞከሩ ድሃ ገበሬዎቸን፣ ዘማቾቸን፣ ተራማጅ የመሬት ይዞታ ወኪሎቸን በማስጨረስ ላይ ይገኛል::

ነገር ግን ይህ የጭቁኖች አርር አለተሰማምና አብዮታችንን ከመገስገስ፣ ጭቁኖችን ከማሸ
ነፍ የሚያገዳቸው ከእንግዲህ ምንም አይነት ሃይል የለም::የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ባላቸው አ
ቅም፣ እስከፀጉራቸው የታጠቁትን አድሃሪያች አመጽ እየመከቱ ከፍተኛ ትምህርት በመቅሰም ላይ ና
ቸው::ከራሳቸው ሌላ የሚተማመኑበት ምንም ሃይል እንደሌለ ገብቷቸዋል::ስለዚህም በዚህ በያዙት
አብዮታዊ ትንንቅ ገፍተው፣ ድርጅቶቻቸውንም አጠንክረው፣ የሚያስፈልጋቸውንም ትጥቅ ''ከደርጉም
ሆነ ከደርጉ ውጭ'' ፈልገው በአብዮታዊ አመጽ የመንግስትን ስልጣን እጃቸው ያስገባሉ::

እንኳን የትጥቁን ነገር አንስተን ይቅርና፣ ድርጅቶቻቸውን እንኳን ያጠናከሩ ስንል
''አሁን ካሉትና በአጭር ጊዜ ሊቋቋሙ ከሚችሉት'' ድርጅቶች በአስቸኳይ እንመራረጥ እያላችሁ
ለምትለፍፉት አድርባዮች ይህ ጎዳና ረዥም ይመስላችሁ ይሆናል::ግን ለአብዮታዊ ድል ያለው መን
ገድ ይኸው ብቻ ነው::የኢትዮጵያ ጭቁኖችም፣ ችግራቸውንና ብሶታቸውን ብቻ ሳይሆን የታጠቁ አድ
ሃሪያችን እብሪትና አመጽ ከጭቁኖች ጎን ሆነው በመከራ በመክፈል ላይ ያሉት ዘማቾችም ተራማጆችም
ይህንን ሁሉ ሃቅ ተገንዝበውታል::ከአዲስ አበባ ሚልዮን አብዮታዊ አዋጅ ቢወጣ ስራ ላይ ይውላል
ማለት አይደለም::ስራ ላይ የመዋሉ ጉዳይ ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ከነሱም ጋር በሺህ
የጥቅም ክሮች የተሳሰረውን የአስተዳደር አውታር በጭቁን ህዝቦች አመጽ በየመንደሩና በየሰርቻው
መደምሰስን ይጠይቃል::እነዚህ ፀረህዝቦች እስካልተደመሰሱ ድረስ ''በቢሮክራሲያዊ ምርጫ''
ወኪሎቻችሁን ምረጡና ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አቋቁሙ፣ በመንደራችሁ መደምሰስ ያቃታችሁን ጠ
ላት እኛ ከሩቋ አዲስ አበባ እንደመስስላችኋለን እያሉ ከትግል ሊያዘናጉአቸው የሚፈልጉትን አ
ወናባጆች ከእንግዲህ አያዳምጡአቸውም::የኢትዮጵያ ጭቁኖች በመንደራቸው ጣፊያ እየተነሱ፣ ከአዲስ
አበባ ታናሽና ታላቅ ስደድላን በለው ወኪል የሚልኩበት ምንም ምክንያት የላቸውም::

ሁኔታው እንደዚህ ሆኖ ሳለ፣ የመታጠቅና በአብዮታዊ አመጽ ፀረህዝቦችን ደምስሶ አብዮታዊ
መንግስትን የማቋቋሙ ተግባር ከፊታችን ተደቅኖ ሳለ፣ የታጠቁ አድሃሪያችና ፖሊሶች በድሃው ገበሬ፣
በዘማቹ፣ በተራማጁ ላይ መረን ተለቀቀው እንዳበደ ውሻ በሚናከሱበት በአሁኑ ጊዜ፣ ይህንን አ
ንገብጋቢውን የትጥቅ ጉዳይ ችላ ብላችሁ ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' የሚለውን አድሃሪ መፈ
ክር በአንቀልባ አዝላችሁ ማላዘን ተቻላችሁ::

እኛ ግን፣ ለኢትዮጵያ ወጣቶች፣ ወዝአደሮችና ጭቁን ህዝቦች፣ ያለአንዳች አወደዳባይነትና
አድርባይነት ትግላችሁን የአንድን ህዝብ ነፃነት ለመሰለ ቁምነገር የሚደረግ ታሪካዊ ትግሉ
በመሆኑ ረዥምና የተወሳሰበ እንደሆነ ያለመታከት እናስገነዝባለን::እስከዛሬው ግን አድርባዮችና
አወናባጆች አንድ ነገር ልብ በሉ::አሁን በምትነዙት ውዥንብር ታግዘው መስፍንቶ፣ መኳንንቶ
ኢምፔሪያሊስቶች የሚጠነስሱት ስራ ተሳክቶ፣ ህዝቡም ከትጥቅ ትግል አይኑ ወደምርጫ ተስቦ፣ የና
ንትን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ''ይመርጥላችሁ'' ይሆናል::ነገር ግን ይህንን ስራ እንደህዝ
ባዊ ድል ቆጥረላችሁ፣ የኢትዮጵያ ተራማጆች የትግል ትጥቃችንን አንፈታም::ህዝቡ እንዲደራጅና
እንዲታጠቅ የምናደርገውን ቅስቀሳና ትግል ፋታ ሳንሰጣችሁ እንቀጥላለን::የምትጭኑብንን
''ቢሮክራሲያዊ'' መንግስታችሁን በአብዮታዊ ህዝባዊ አመጽ ተቋቁመን፣ የኢትዮጵያን ጭቁን ህዝ
ቦች ፈላጭቆራጭና አብዮታዊ አገዛዝ በህዝብ ጠላቶች መቃብር ላይ እንመሰርታለን::አድሃሪያችም
አድርባዮችም ለዚህ ጥርጥር አይገባችሁ::

በመጨረሻ ላይ ለአንባቢያችን ልናስገነዝብ የምንፈልገው አንድ ነገር አለ::''የሰፊው
ህዝብ ድምጽ'' የጊዜው ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም እ
ንደሆነና ዋናውም ቅራኔ በነዚህና በኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ መካከል እንደሆነ አመልክቶአል::በነዚህ
ዋና ጠላቶች ላይ የሚነሱ ሃይሎች በሙሉ በትግል ሊተባበሩ እንደሚችሉና መተባበርም እንዳለባቸው
ያምናል::የተራማጆችም ተግባር እርስ በራሳቸው መነካከስ ሳይሆን እነዚህን ዋና ጠላቶች በተባበረ
ሃይል ለመደምሰስ ሰፊውን ህዝብ ማደራጀትና ማዘጋጀት እንደሆነ ግልጽ ነው::ለመተባበርና የትግል
አንድነት ለመመስረት ግን ውዥንብርን አስወግዶ የጠራ የፖለቲካ መስመር መቀየስ እጅግ አስፈላጊ
ነው::ውዥንብር ነዢያችንም ማጋለጥና መታገል የሚያስፈልገው ለዚሁ ነው::በ''ቢሮክራሲያ''ላይም
ሆነ በሌሎች ተመሳሳይ ቡድኖች ላይ የምናቀርበው ሂስና ማጋለጥ የ''ቢሮክራሲያ'' አዘጋጆች
እንደሚያደርጉት፣ ተራማጆችን ለመከፋፈል፣ የህዝቡን ትግል ለማዳከም፣ ተራማጆችን በስም እየጠሩ
ለጠላት አሳልፎ ለመስጠት ሳይሆን፣ በ''ቢሮክራሲያ'' ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ካሉት ሃቀኛ ተ
ራማጆች ጋር የትግል አንድነት ለመመስረት ነው::ዛሬ ይህን ባናደርግ ወደፊት በአብዮቱ ላይ ለ
ሚፈጠረው ተጨማሪ ችግር ተጠያቂያች መሆናችን አይቀርም::በ''ቢሮክራሲያ'' ውስጥ ያሉ ሃቀኛ
ተራማጆች ጋዜጣቸው የሚነዛውን ውዥንብር ማስወገድ አለባቸው::አብዮታዊ ግዴታቸው ነው::

አቅማችን የተወሰነ በመሆኑ ብዙ ቅጂያችን
አሳሰራጨንምና በይዘቱ የምትስማሙ አንባቢ
ያን በሙሉ አንብባችሁ ላላነበቡ ብታስተላ
ልፉ፣ ከተቻለም ጋዜጣው የሚበራከትበትን
ዘዴ በየፊናችሁ ብትፈልጉ ለትግላችን ይበ
ጃል::

አድሃሪያችም፣ አድርባዮችም በህዝባዊ አመጽ ይወድማሉ

የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ያሸንፋሉ::